# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 193 ጥር 17 2004 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በጋምቤላ እየተፈፀመ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲቆም እና ወንጀለኞች ለፍርድ እንዲቀርቡ ይታገላል። የጋምቤላ ለም መሬትን በማደል ሃብታሞች ይበልጥ ሃብታም እንዲሆኑ፤ ድሆች ደግሞ የእለት ጉርሳቸውን ሳይቀር እንዲያጡ እየተደረገ ያለውን እኩይ ድርጊት በጥብቅ ይኮንናል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ግንቦት 7 ሶስተኛ አመታዊ ጉባኤውን በማካሄድ ላይ እንደሚገኝ ገለጸ

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ካለፈው ሳምንት ጥር 12 ቀን ጀምሮ ሶስተኛ አመታዊ ጉባኤውን በተሳካ ሁኔታ እያካሄደ መሆኑን ከንቅናቄው የህዝብ ግንኙነት ክፍል ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ ማስታወሻ ገልጿ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የክልል ተወካዮችን ጨምሮ የአውሮጳ፤ የአፍሪካ፤ የኤሲኢያ፤ የመካከለኛው ምስራቅ፤ የካናዳ፤ የሰሜን አሜሪካና የአውሮጳ ተወካዮች እየተሳተፉበት ነው በተባለው በዚህ ሶስተኛ ጉባኤ ላይ በዋንኛነት መነጋገሪያ አጀንዳ የሆነው ከወያኔ ጋር እየተካሄደ ያለው የጸረ ዘረኝነት ትግል ይበልጥ ተጠናክሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ ግቡን ሊመታ የሚችልበትን ድርጅታዊ አቅም ስለማጎልበት እንደሆነ ተያይዞ የደረሰን መረጃ ያስረዳል።

የትግላችን ዋና አላማ በየጊዜው የሚፈራረቁ አገዛዞች ለዘመናት የነፈጉንን ፍትህ፤ እኩልነትና ነጻነት በአገራችን እንዲሰፍን በማድረግ የመንግሥት ሥልጣን በህዝብ ምርጫ ብቻ የሚያዝበትን የዲሞክራሲ ሥርዓት መገንባት ነው የሚለው ግንቦት 7፤ አሁን ሥልጣን ላይ ያለው የወያኔ አገዛዝ በዘረጋው ዘረኛ ድርጅታዊ መዋቅር የአገራችን ሉአላዊነትና የህዝቦቿ የወደፊት ዕጣ ፋንታ የማያሳስባቸው ከአንድ አካባቢ የተውጣጡ ጎጠኞች ቁልፍ ቁልፍ የመንግሥት ሥልጣንና የኢኮኖሚ ተቋማትን እንዲቆጣጠሩ በማድረግ እየፈጸመ ያለውን ዘረፋና አገርን ለባዕዳን የመሸጥ ዘመቻ ማስቆም ቅድሚያ የሚሰጠው ትግል መሆኑን መላው አባላቱ ተረድተው ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋ ዕትነት ሁሉ በመክፈል ትግሉን ከዳር የማድረስ ውሳኔ በዚህ ጉባኤ ይተላለፋል ተብሎ እየተጠበቀ እንደሆነ ከህዝብ ግንኙነት የደረሰን ዜና አስታውቆአል።

የንቅናቄው ጉባኤ እስከዛሬ ባካሄደው ስብሰባ አዲሱን የድርጅቱ የትግል ስትራቴጂ ሠነድና የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ረቂቁ መርምሮ እንዲጸድቅ ወስኖአል ተብሎአል። ጉባኤው በዛሬው እለት ማምሻውን የጋራ መግለጫ በማውጣት እንደሚጠናቀቅ ለማወቅ ተችሎአል።

## የወያኔ ፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሶስተኛ ወንጀል ችሎት ባለፈው ሀሙስ በሶስት ጋዜጠኞችና ሁለት ፖለቲከኞች ላይ ከአስራ አራት አመት እስከ ዕድሜ ልክ የሚደርስ ጽኑ እስር ቅጣት አስተላለፈ። ውሳኔው አለም አቀፍ ተቃውሞ እያስከተለ ነው

ህዝብዊ ድጋፍና አመኔታ ሳያገኝ ላለፉት 20 አመታት በጠመንጃ አፈሙዝ አገር እየገዛ ያለው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ህዝባዊ ተቃውሞ ሊቀሰቂሱብኝ ይችላሉ በማለት ፈርቶ ከርቼሌ ባወረዳቸው ንጹሃን የአገሪቱ ዜጎች ላይ እያደረሰ ያለው ኢፍትሃዊነት በመቀጠል ከትናንትና ወዲያ ሃሙስ በ3 ጋዜጠኞችና ሁለት ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባላት ላይ ከ14 አመት እስከ ዕድሜ ልክ የሚደርስ ጸኑ እስራትና የገንዘብ ቅጣት መተላለፉ ከፍተኛ የሆነ አለም አቀፍ ተቃውሞ እያስከተለ ነው።

"ህገመንግሥቱን በሃይል ለመናድ፤ የአገሪቱን መሰረተ ልማቶች ላይ ጥቃት ለማድረስና ኤሌክትሪክ መስመሮችን ከጥቅም ውጪ ለማድረግ ተንቀሳቅሰዋል" ተብሎ የተከሰሱ እነዚህ ንጹሃን ዜጎች፤ አንዳቸውም የተመሰረተባቸውን ክሶች ለመፈጸማቸው መረጃ ያልተገኘባቸው እንደሆነ ሲታወቅ፤ ለሆዳቸው እንጂ ለሰብዕናቸው ወይም ለተሰማሩበት ሙያና ለአገሪቱ የፍትህ ሥርዓት ቅንጣት ታህል ደንታ በሌላቸው ካድሬ ዳኞች አማካይነት ከመለስ ዜናዊ ጽ|ቤት በቀጥታ የተሰጠ የፍርድ ትዕዛዝ ተግባራዊ ሊሆንባቸው ችሎአል።

ከመለስ ዜናዊ ጽ|ቤት በተላለፈው የፍርድ ውሳኔ መሰረት ከ14 አመት እስከ ዕድሜልክ ጽኑ እስራት የተፈረደባቸው 1ኛ የፈጠራ ክሱ በሌለበት የታየው አንደኛ ተከሳስ ኤልያስ ክፍሌ ሲሆን የተሰጠው ቅጣት የእድሜ ልክ እስራት ነው።

የ14 አመት ጽኑ እስራት ፍርድ የተሰጠው 2ኛ ሰው በወያኔ አፈና ምክንያት ሀትመቱ በቅርቡ የተዘጋው የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ ውብሸት ታዬ ሲሆን ከ14 አመት እስራት በተጨማሪ 33,000 ብር ቅጣት ተጥሎበታል። ሌላዋ ጋዜጠኛ የፍትህ ጋዜጣ አምደኛ የሆነቸው ወጣት መምህርት ርዮት አለሙ ስትሆን እርሷም እንደውብሸት የአስራ አራት አመት ፅኑ እስራትና የ36,000 ብር ቅጣት ተፈርዶባታል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## መድረክ የወያኔ አገዛዝ የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣውን ዓዋጅ በመቃወም ዜጣዊ መግለጫ ሰጠ

መድረክ የተባለው የ8 ፓርቲዎች ህብረት በትናንትናው ዕለት በጽ|ቤቱ በጠራው ጋዜጣዊ መግለጫ ወያኔ በቅርቡ ያወጣውን የከተማ ቦታን በሊዚ የማስያዚ አዋጅ በጽኑ ተቃውሞታል። መድረክ አዋጁን በመቃወም በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ የአመራር አባላት የሆኑት ዶ/ር ሞጋ ፍሪሳ፣ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ ዶ/ር መረራ ጉዲና፣ አቶ ገብሩ አስራት፣ አቶ ገብሩ ገብረማርያም እና ሌሎችም ከጋዜጠኞች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ሰጥተዋል::

በጋዜጣዊ መግለጫው ወቅት" የኢህአዴግ ካድሬዎች ከምንም ነገር በላይ ገንዘብ እንዴት እንደሚሰበስብ ያውቃሉ ያሉት ዶ/ር መረራ ጉዲና ከዚህ ቀደም በግላቸው መሬት ሲጠበቸቡ ነበር፤ አሁን ደግሞ የገንዘብ ፍላጎቱን ማሟላት ያቃተው የኢህአዴግ መንግሥት የአዲስ የመሬት አዋጅ አውጥቶ ዜጎችን እያደኸየ ሃብት በመንጠቅ ኢኮኖሚውንና ፖለቲካውን በሞኖፖል ተቆጣጥሮ እየለመኑት እንዲኖሩና ዘወትር እንዲቆጣጠራቸው ይፈልጋል ብለዋል::

ዶር መራራ ቀጥለውም፤ በፊውዳሉ ጊዜ እንደነበረው የኢህአዴግ መንግሥት ዜጎችን ከአካባቢያቸው ሲያፈናቅል ብትፈልጉ ጣራና ግርግዳውን ሸጣችሁ ሂዱ፤ መሬቱ የመንግሥት ነው እያለ ያሸፍባቸዋል የደርግ መንግሥት እንኳ ይሄን አላደረገም፤ እንደውም ሰው ከባንክ ብድር እየወሰደ ቤት እንዲሰራ ያመቻች ነበር እንጂ ጣራና ግርግዳ ነው የእናንተ እያለ ዜጎችን አላፈናቀለም:: ምክንያቱም ሰው ቤቱን የሚሰራው መሬት ላይ ነው እንጂ አየር ላይ አይደለም፤ የቤት ባለቤትነት ከመሬት ተነጥሎ አይታይም፤ ኢህአዴግ ግን ዜጎችን ሃብታቸውን እየነጠቀና እያደኸየ ሰጪና ቀሚ ሆኖ ነው መግዛት የሚፈልገው፣ ስለዚህም ይሄን የመሬት ዓዋጅ መድረክ ይቃወመዋል:: አንድ ትውልድ መሬት ላራሹ ሲል ነበር የታገለው ኢህአዴግ ግን መሬት ለኢንቨስተሩ በሚል ለውጦታል ብለዋል::

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ዘረኛው መለስ ዜናዊ ወደ ሱማሊያ መልሶ ካዘመታቸው የመከላኪያ ሠራዊት 10 ወታደሮች በአልሸባብ መገደላቸው ተዘገበ

ዘረኛውና አምባገነኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአገር ውስጥ ያጣውን የህዝብ ድጋፍ ከውጪው ማህበረሰብ ለማግኘት ሲል ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ሱማሌ ካዘመታቸው የመከላኪያ ሠራዊት አባላት ውስጥ 10ሩ በአልሸባብ ተዋጊዎች መገደላቸውን የተለያዩ አለም አቀፍ ሚዲያዎች ዘግበዋል።

ወያኔ ድህረ ምርጫ 97 በአዲስ አበባና ሌሎች ትላልቅ ከተሞች በህዝባችን ላይ በፈጸመው ጭፍጨፋ የአለም አቀፉ ህብረተሰብ ውግዘት ሲበዛበት ትኩረት ለማስቀየር ሲል ሰራዊቱን ወደ ሱማሌ በማዝመት ለበርካታ ንጹሃን ሱማሌዎችና ቁጥራቸው እስከዛሬም ቢሆን ይፋ ያልሆነ የራሱ ወታደሮች መገደል ምክንያት እንደሆነ ይታወቃል።

በሰሞኑ የተገደሉትን 10 የመከላኪያ ወታደሮችን አስመልክቶ የሶማሊያ ታጣቂ ሀይል የሆነው አልሸባብ እንደገለጠው ጥቃቱን የፈጸመው በለደወይን እየተባለች በምትጠራ የሶማሊያ ግዛት ነው። የወያኔ የይስሙላ ፓርላማ እንኳ ሳያውቀውና ሳይፈቅደው ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ሱማሊያ የተላከው ሰራዊት ባለፈው ወር የበለደወይን ከተማን ከአልሸባብ በመንጠቅ ተቆጣጦሮ እንደነበር የተዘገበ ሲሆን፤ የድሃን ልጆች በሰው አገር ጦረነቶች እየማገዱ ከአለም አቀፉ የመንግሥታት ድርጅት በውጪ ምንዛሪ ገንዘብ እያፈኑ ያሉት የወያኔ ሹሞች አዲጋው ከመድረሱ በፊት ከተማውን ለአፍሪካ ህብረት ሰራዊት ለማስረከብ በዝግጅት ላይ ነበርን ሲሉ መናገራቸው ተዘግቦአል።

ወያኔ ባዘመተው የመከላኪያ ሰራዊት ወታደሮች ላይ የደረሰው ይህ ጥቃት የተፈጸመው አንድ አጥፍቶ ጠፊ ወታደሮች ወደ ሰፈሩበት ካምፕ በመሄድ በፈጸመው ጥቃት ነው ተብሎአል። አንድ አይን እማኞች ገለጻ በአደጋው ምክንያት የኢትዮጵያ ወታደሮች የሚኖሩበት ህንጻ በጥቃቱ ተደረማምሰዋል።

ጎሬቤት ሱማሊያ ካለፉት ሁለት አሥርተ አመታት በላይ በእርስ በእርስ ጦርነት የወደመችና አሁንም በጦርነት ውስጥ ያለች አገር መሆኗ እየታወቀ፤ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ተቃዋሚዎቹን መጠጊያ ለማሳጣት ባለው ስትራቴጂ በሞግዚትነት የሚተዳደር ጊዜያዊ መንግሥት በሞቃዲሾ እንዲቋቋም በማድረግ ጦርነቱ እንዳያባራ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝ ገለልተኛ የሆኑ አለም አቀፍ ድርጅቶች ይከሳሉ።

## ጋምቤላ ትጣራለች፤ ምላሽ እንስጥ!!!

በምዕራቡ የአገራችን ክፍል -ጋምቤላ - እሮሮ በዝቷል!!!

ለምለሟ ጋምቤላ ለነዋሪዎቿ ሲዖል፤ ለመለስ ዜናዊ ምርጦች ግን ገነት ሆናለች። ለምለሟ ጋምቤላ ነዋሪዎቿ የሚራቡባትና የሚታረዙባት፤ ባህር ተሻግረው የመጡ ቱጃሮች ግን ሲሳይ የሚያፍሱባት ምድር ሆናለች። ለምለሟ ጋምቤላ ነዋሪዎቿ ለእስርና እንግልት፣ ለመፈናቀልና መሰደድ፣ ሲከፋም ለሞት የሚዳረጉባት፤ ቱጃሮች ግን በከርሰ-ምድር ሃብቷ ሰበብ የሚራኮቱባት ክልል ሆናለች። ጋምቤላ ፍቅረ ንዋይ አዕምሮዓቸውን ያነወዛቸው ዘረኞች ባድማ ሆናለች። የትግራይ ገዢ ጉጅሌ፣ ጋምቤላ ውስጥ ገንዘብ እንጂ ሰው ያለ መሆኑ አይታወቀውም።

በጋምቤላ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ሰቆቃ ቃላት ሊገልጹት ከሚችሉት በላይ ነው። የዛሬ አስር ዓመት የአኝዋክ ወንዶች በመለስ ዜናዊ የጦር ሠራዊት አባላት እየታደኑ ተገደሉ፤ ህፃናት ታረዱ። ሴቶች በባሎቻቸውና በልጆቻቸው ፊት ተደፈሩ። አንዳንዶቹም ተደፍረውም ተገደሉ። መንደሮች በእሳት ጋዩ። ሞትና እልቂት በመላው ጋምቤላ ምድር ተዘራ። በጥቂት ቀናት ውስጥ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ አኝዋኮች ህይወታቸውን አጡ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አስከ አሁን ጥቃቱ አላባራም። በሺዎች የሚቆጠሩ አኝዋኮች በግፍ ተገድለዋል። በአስር ሺዎች የሚቆጠሩት ደግሞ የማይጠገን የአካልና የመንፈስ ጉዳት ደርሶባቸዋል። በህይወት የተረፉት ጥቂቶች በወያኔ እስር ቤቶች ውስጥ እየማቀቁ ነው፣ አሊያም ተሰደዋል። ጋምቤላ ለአኝዋኮች ባይተዋር ሆናለች።

በአንፃሩ ደግሞ ለመለስ ዜናዊ ዘረኛ ቡድን እና ተላላኪዎቹ ጋምቤላ የወተት ላም ነች። የመለስ ዜናዊ የግል ዘመዶችና ሸሪኮች የጋምቤላን መሬት በብላሽ ተመርተው ደኑን እየማገዱ ከሰል በመሸጥ ከብረዋል። የደኑ መራቆት አያሳስባቸውም። የገበሬዎች መፈናቀል አያገባቸውም። መከረኞቹ አኝዋኮች ግን ከትውልድ ቀያቸው ተፈናቅለው መውደቂያ አጥተዋል። እርሻቸውና የግጦሽ መሬታቸው በትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላት አልያም ከሩቅ አገራት በመጡ ቱጃሮች ተነጥቀዋል። አቤት የሚባልበት ቦታ የለም።

ጄኖሳይድ ዎች፣ ሂውማን ራይትስ ዎች፣ ተመራማሪዎች፣ ለጋሽ አገራት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ የረድኤት ድርጅቶች ስጋታቸውን ይገልፃሉ፤ ይመክራሉ፤ ያስጠነቅቃሉ፤ ያስገነዝባሉ፤ ሲብሰባቸውም ይጮሃሉ። የሚሰማቸው ግን የለም። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ግንባር ቀደም መሪዎችና ጀሌዎቹ በሃብት ቅርምት ላይ ናቸው።

በዚህ ሁሉ ግፍ መሃል ጋምቤላ ምጥ ላይ ነች። ጋምቤላ ለበደሏ ቤዛ ሊሆኑ የቆረጡ ልጆችን መውለድ ቀጥላለች። እናም የወያኔ መፈንጫ ሆና አትቀርም። አዎ! ጋምቤላ ምጥ ላይ ነች፤ ለእርዳታም ትጣራለች። ለጋምቤላ መድረስ ለኢትዮጵያም መድረስ ነው። የጋምቤላ እጣ ፈንታ የኢትዮጵያም እጣ ፈንታ ነው። ለጋምቤላ ጥሪ ምላሽ እንስጥ!!!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በጋምቤላ ዜጎቻችን ላይ እያደረሰ ያለው በደል ያንገበግበዋል። በግንቦት 7 እምነት ከአኝዋኮች ጋር የተገደልነው፣ የተገፋነው፣ የተደፈርነው፣ የተዋረድነው ሁላችንም ነን። በጋምቤላ ነዋሪዎች ላይ የደረሰው በደል በደላችን፤ ህመማቸው ህመማችን ነው። ከጋምቤላ ጋር እየተመዘበረች ያለችው ኢትዮጵያ ነች።

በጋምቤላ ክልል ውስጥ እየተፈፀመ ያለውን ግፍ በማጋለጥ ረገድ እስካሁን የአካባቢው ተወላጆች እያደረጉት ያለውን ጥረት ግንቦት 7 ያደንቃል። እየተደረጉ ያሉት ጥረቶች እንዲቀናጁ የበኩሉን አስተዋጽዖ ያደርጋል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በጋምቤላ እየተፈፀመ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲቆም እና ወንጀለኞች ለፍርድ እንዲቀርቡ ይታገላል። የጋምቤላ ለም መሬትን በማደል ሃብታሞች ይበልጥ ሃብታም እንዲሆኑ፤ ድሆች ደግሞ የእለት ጉርሳቸውን ሳይቀር እንዲያጡ እየተደረገ ያለውን እኩይ ድርጊት በጥብቅ ይኮንናል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ የትግላችን ትኩረት የዚህ ሁሉ መከራና ግፍ ምንጭ የሆነውን ወያኔን በማስወገድ በምትኩ ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት፤ ሕዝቧ በእኩልነት፣ በአንድነትና በሰላም የሚኖርባት ኢትዮጵያን በመገንባት ላይ ማነጣጠር ይገባዋል ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የወያኔ ፌዴራል ፍርድ ቤት በነጻነት ታጋዮቹ እነ አንዱአለም አራጌና እስክንድር ነጋ ላይ የተጠበቀውን የጥፋተኝነት ብይን ሰጠ። ብይኑ ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመድረሱ በፊት የተፈጸመ መሆኑን ተከሳሾች ተናገሩ

"በህጋዊ ፓርቲ ጥላ ስር ተከልለው የመንግሥት ባለስልጣናትን ለመግደል፣ መሠረተ ልማቶችን ለማውደም እና ከአሸባሪ ቡድኖች ጋር አንድ ላይ በማበር ሕገመንግሥቱንና ሕገመንግሥታዊውን መንግስት ለመገልበጥ በሀገር ውስጥና በውጭ አገራት አሲረው ተንቀሳቅሰዋል" በሚል የፈጠራ ክስ የተከሰሱት እነ አቶ አንዱአለም አራጌ፤ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና ሌሎች 22 ሰዎች ላይ የወያኔ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ሦስተኛ ወንጀል ችሎት ከትናንት ወዲያ ረቡዕ የጥፋተኝነት ብይን እንደሰጠባቸው ለማወቅ ተችሎአል።

ከመለስ ዜናዊ ጽ|ቤት በቀጥታ በተላለፈውና በነሺመልስ ከማል አስፈጻሚነት አቃቤ ህግ ተብዬው ተቋም ክስ አድርጎ ባቀረባቸው ስድስት ክሶች ውስጥ የይስሙላ ፍርድ ቤቱ ህግ ያለ ለማስመሰል ያህል ሁለቱን ውድቅ አድርጎ በአራቱ ክሶች 1ኛ አንዷለም አራጌ፣ 2ኛ ናትናኤል መኮንን፣ 3ኛ ዮሐንስ ተረፈ፣ 4ኛ ሻምበል የሸዋስ ይሁንአለም፣ 5ኛ ክንፈሚካኤል ደበበ፣ 6ኛ ምትኩ ዳምጤ፣ 7ኛ እስክንድር ነጋ እና 8ኛ አንዷለም አያሌው ጥፋተኛ ናችሁና ክሱን ተከላከሉ ሲባሉ፣ ከአገር ውጪ የሚገኙት ተከሳሽ 1ኛ አንዳርጋቸው ጽጌ፣2ኛ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ፣ 3ኛ ውቤ ሮቤ፣ 4ኛ መስፍን አማን፣ 5ኛ ዘለሴ ጸጋ ስላሴ፣ 6ኛ ፋሲል የኔአለም፣ 7ኛ አበበ በለው እና 8ኛ አባንግ ሜቶ በ6ቱም ክሶች ጥፋተኞች ናቸው ተብለዋል።

የወያኔው ፍርድ ቤት በዚህ ዙር የዳኝነት ዲራማው ትርዕቱን ለማሳመር ሲል ገለልተኛና ሙያተኛ መስሎ ለመታየት ከ24ቱ ተከሳሾች 12ኛውን ተከሳሽ ኤፍሬም ማዴቦን 17ኛውን ተከሳሽ አበበ ገላው፣ 18ኛውን ተከሳሽ ንአምን ዘለቀን፣ 19ኛውን ተከሳሽ ኤልያስ ሞላን፣ 20ኛውን ተከሳሽ ደሳለኝ አራጌንና 21ኛውን ተከሳሽ ኮ/ል አለሁበል አማረ አቃቤ ሕግ ከጥርጣሬ በዘለለ በቂ ማስረጃ ሊያቀርብ ባለመቻሉ ነፃ ናቸው ብሎ ወስኖአል። ወሳኔው በንባብ በተሰማበት ወቅት ችሎቱን ለመከታተል በሥፍራው የነበሩት ሁሉ በሳቅ እንደተዋጡ ዘጋቢያችን ከላከው ዘገባ ለማወቅ ተችሎአል።

ለአለፉት አምስት ወራት በኢህአዴግ መንግሥት በእስር ላይ የሚገኘው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር አቶ አንዷለም አራጌ "ከታሰርንበት ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ በደሎችና ሰቆቃ በመንግስት ቢደርስብንም ይሄ ፍርድ ቤት አቤቱታችንን ሰምቶ የሚደርስብንን በደል ሊያስቆምልን አልቻለም፤ እውነት ፍርድ ቤቱ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለፍትህ የሚሰራ ከሆነ የተፈጸመብንን በደል አይቶ እርምጃ ሊወስድ በተገባ ነበር፡፡ ነገር ግን ከፍርድ ቤት በፊት ከጠቅላይ ሚንስትር መለስ ጀምሮ ፍርድ ከቤተመንግሥት በግለሰቦች ሲሰጥ ማየታችን አያስገርመንም በደንብ የታወቀ ጉዳይ ሆኗልና፡፡ ለዚህም ነው ክሱ ከመመስረቱ በፊት አቶ መለስ በኢቲቪ ፍርድ ሰጥተው ያወሩትን ነው ፍርድ ቤቱ እየደገመው ያለው፣ ኢቲቪው እየሰራው ያለው ፕሮፓጋንዳ ይሄንኑ ነው' ብሎ ሲናገር መለስ ዜናዊን መከላከል ተቀዳሚ ተግባራቸው ያደረጉት ዳኞች በተግሳጽ አስቁመውታል ተብሎአል፡፡

5ተኛ ተከሳሽ የሆነው ክንፈሚካኤል ደበበም በበኩሉ "ለፍርድ ቤቱ አቤቱታ አለኝ ብሎ በመነሳት "የኤርትራ መንግስት ተላላኪ የሚል ክስ ቢቀርብብኝም ፍርድ ቤቱ በማስረጃ ተደግፎ ባለመቅረቡ ውድቅ አድርጎታል ፣ ነገር ግን የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን በትላንትናው እለትም ከአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር አያይዞ እያቀረበኝ እየወነጀለኝና ሥሜን እያጠፋው ነው" ማለቱ ተዘግቦአል።

ሆኖም ፍርድ ቤት ተብዬው የካድሬዎች ችሎት ሰብሳቢ የተፈጸመባቸውን ኢፍትሃዊነት ለመግለጽ የሞከሩትን "አቶ አንዷለም አራጌንና አቶ ክንፈሚካኤል ደበበን ችሎት እየተጋፋችሁና በምትናገሩት ንግግር ዘወትር የፍርድ ቤቱን ልዕልና እየጣሳችሁ በመሆኑ ከዚህ በኋላ ሊያስቀጣችሁ የሚችል መሆኑን እንድታውቁ በማለት ሁለተኛ እንዳይናገሩ ማስፈራራቱ ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

በችሎቱ ማብቂያ ላይ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ድምጹን ከፍ አድርጎ "እኔ በሀሰት የተወነጀልኩ ንጹህ ሰው ነኝ፣ ከግንቦት 7 ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለኝም፤ ይህን ህዝብ እንዲያውቅልኝ እፈልጋለሁ፡፡ በሀሰት ከተመሰረተብኝ ክስ ነፃና ንጹህ ነኝ" ሲል ተሰምቶአል::

የፍርድ ቤቱን ውሎ የተከታተሉ አንድ የህግ ባለሙያ ለዘጋቢያችን እንደተናገሩት የአገራችን ፍትህ ሥርዓት እንዲህ እንደአሁኑ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዘመን የተዋረደበትና የዘቀጠበት ወቅት በታሪካችን አልነበረም ፤ ከወያኔ ፍርድ ቤት ፍትህ መጠበቅ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ሆኖአል።

## እራሱን ልማታዊ መንግሥት ነኝ የሚለው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ . . . (ከገፅ 4 የዞረ)

ዘረኛው መለስ ዜናዊ ከአምስት አመታት በፊት ረሀብ ታሪክ ይሆናል፣ ከ17 አመታት በፊት ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ በቀን ሶስት ጊዜ እንዲበላ እናደርገዋለን ማለቱ ይታወሳል። ወያኔ ስልጣን ላይ ከመጣ ወዲህ በየአመቱ ቁጥራቸው እስከ አሥራ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ወገኖቻችን እየተራቡ በአለም አቀፍ የምግብ እርዳታ ይተዳደራሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከአመት አመት በአለም ባንክና በሌሎችም ለጋሽ ድርጅቶች በሚሰፈርላቸው ስንዴ ብቻ የሚኖሩ ፣ ሴፍቲኔት በሚባለው ፕሮግራም የታቀፉ 7 ሚሊዮን ዜጎች በአገሪቱ ውስጥ መኖራቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ወያኔ በተፈጥሮ ደኖቻችን ላይ በደቡብና በኦሮሚያ ያደረሰውን አይነት ውድመት በአሁን ሰዓት በጋምቤላና በቤኔሻንጉል ክልሎች አጠናክሮ እንደቀጠለ የተለያዩ አለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ ባለሚሎች እየገለጹ ነው።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

# ወይ ነዶ ኢትዮጲያ! ማን ነው ተጠያቂው?

## የግንቦት7 ጋዜጣ ቁጥር 28 ላይ ወጥቶ የነበረ ርዕሰ አንቀጽ

ስድስት ሚሊዮን ሕጻናት፣ ከአምስቱ ሕፃናት ኣንዳቸው አባት እናት የሌላቸው የሙታን ልጆች፣ የተቀሩት ሕጻናት ከሙታኑ ልጆች ልዩነት በሌለው የኑሮ መቃብር ከነወላጆቻቸው የሚኖሩባት ሃገር፣ ኢትዮጲያ። ኣስራ ኣራት ሚሊዮን፣ ሕዝብ ከስድስቱ ዜጋ አንዱ፣ በውጭ መንግስታት እርጥባን ስጋን ከነፍሱ አጣብቆ የሚያድርባት ሃገር፣ ኢትዮጲያ። ሶስት ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ፣ ከሃያ አምስቱ ዜጋ አንዱ ከአስከፊው የኤድስ በሽታ ጋር የሚኖርበት፤ በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠር በሳንባ ነቀርሳ በወባ፣ በተስቦና ከአለማችን በጠፉ በሽታዎች የሚያልቅበት ሃገር፣ ኢትዮጵያ።

ወገኖቻችን ለአገራችን ሕልውና መከበርና ለነጻነታችን መጠበቅ በታሪካቸው የከፈሉትን መስዋዕትነት የሚመጥን ስልጣኔ አልተቀናጀን፤ ለአርነታቸው ያሳዩትን ቀናኢነት የሚያንጸባርቅ መብት አልተላበስንም በማለት "እምቢ ለጭሰኛነት፣ እምቢ ለገባርነት" ብለው በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ብሩህ ዕምሮ የነበራቸው ወጣት ተማሪዎችና ምሁራን እንደ ቅጠል የረገፉበት፣ መስዋዕትነታቸው ከንቱ ሆኖ፣ በመሳፍንቱና በባላባቱ ምትክ ጥቂት ዘረኛ ደናቁርት ተተክተው ሃገሬውን በሙሉ ገባር ኣድርገው በሚኖሩበት ሃገር፤ ኢትዮጲያ! ለሺዎች ዓመታት ነጻነቱን በከፍተኛ መስዋዕትነት አስጠብቆ የኖረ ሕዝብ ለጥቂት ዘረኞች ባሪያ የሚኖርበት ሃገር፣ ኢትዮጲያ!ስልጣን ከማዕከሉ እጅ ወጥቶ ሕዝብ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት መንደርና ቀበሌ ድረስ ይውረድ፣ ሁሉም ቋንቋውን ባህሉን የሚጠቅምበት የሚያሳድግበት እኩልነቱ ይከበር ለሚል ፍትሃዊ ጥያቄ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ኣልቀው፣ ጥቂት ዘረኞች የሀገሪቱን የፖለቲካ ስልጣንና ምጣኔ ሃብት ተቆጣጥረው በታሪካችን አይተነው የማናውቀው በዘር ላይ የተመሰረተ አስከፊ ዘረፋና መጠቃቀም የሚያካሂዱበት ሃገር፣ ኢትዮጲያ!

ትውልድ እየተፈራረቀ ልጆቹን ያለ አሳዳጊ፣ ወላጆቹን ያለ ጡዋሪ፣ እየተወ፣ ያለስንቅና ያለበቂ ትጥቅ፣ በባዶ እጁና በባዶ ሆዱ በደሙ ዋጅቶ አጥንቱን ኣድቅቆ አብኩቶ ያስጠበቀውን ዳር ድንበር የሚንድ ፈሪ የባንዳ ውላጅ በጀግኖቹ ዙፋን ላይ የወጣበት ሃገር፣ ኢትዮጲያ! የራስዋን አስደፍራ የሌላውን ደፍራ የማታውቅ ሃገር፣ ከኣሜሪካና ከእንግሊዝ መንግስታት ጋር የነበራቸውን ወዳጅነት ሰበብ ሳያደርጉ፣ ዘረኛውን የደቡብ አፍሪካ የታገል የበረውን ኔልሰን ማንዴላን በሚስጥር የውጊያ ትምህርት ለመስጠት፣ በጥቂት የሮዴሺያ ነጮች ለሚረገጡት አፍሪካዊ ወገኖቻቸን፣ በቅኝ ግዛት ተጠፍረው ለሚኖሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአፍሪካ ሃገሮች የዲፕሎማሲና የትጥቅ ድጋፍ በማድረግ አኩሪ ታሪክ የነበራቸው መሪዎች ታሪካቸው ፍትሃዊ ሚዛን ኣጥቶ በተቀሩበት፣ ሕዝብን እየረገጡ ስልጣን ላይ ለመቆየት በሚል ስሌት ለኣሜሪካ እሽክርና አድረው የጎረቤት ሃገሮችን በመውረር በስማችን አሰቃቂ ወንጀል በጎረቤት ወንድሞቻችን ላይ የሚፈጽሙ፣ በሃገራችን ላይ በዙሪያችን የሚገኙ አገሮች ዓይናቸው እንዲቀላ የሚያደርግ በደል የሚሰሩ ከሃዲዎች ስልጣን የያዙበት ሃገር፣ ኢትዮጲያ!

"ሂዱ እናንተ ተከታዮቼ ወደ ኢትዮጲያ ኣቅኑ፣ በእዛ የሚገኘው ብጹእ የክርስቲያን ንጉስ ከክፉ ይጠብቃችሃል" በማለት ነብዩ መሐመድ ቤተሰቦቻቸውንና የመጀምሪያ የእስልምና ተከታዮቻቸውን ወደ ኢትዮጲያ በመላክ የባረከዋትን፣ ለረዥም ዘመን የክርስትናና የእስልምና ተከታዮች በሌሎች ቦታዎች ታይቶ በማይታወቅ መፋቀር በኖሩባት ሃገር ሕዝብ በሃይማኖት እንዲናከስ፣ ሞቃዲሾ ውስጥ ቅዱስ መስጊድ ውስጥ ገብቶ ህጻናትና አረጋውያንን የሚያርድ፣ በደቡብ ኢትዮጲያ በቤተክርስትያን መቅደስ ውስጥ ቀሳውስትንና ምእመናንን በቆንጨራ የሚያስጨፈጭፍ፣ ሕዝብን በዘር ለማናከስ ከሚሰራው እኩይ ተግባር በተጨማሪ በሃይማኖት እንዲባላ የሰይጣን እንጀራ ለመጋገር ሴራ ሲያቦካ የሚያድር ገዥ የተቆለለባት ሃገር፤ ኢትዮጲያ!

ገንዘብ ያለው ዜጋ ገንዘቡን የሚያሸሽባት፣ ዕውቀት ያለው ዜጋ እውቀቱን ይዞ ከኣገር የሚፈረጥጥባት፣ ሙያ ያለው አክብረው ለሚያሰሩት ሌሎች ገቶች ሙያን ለመሸጥ አገር ጥሎ የሚሮጥባት፣ ጉልበ፣ ኣቅሙ ቢኖረውም ዘዴውን ቢያውቅበትም ሁሉም ሃገሩን ጥቂት በዘረፋ ተንደላቀው ለሚኖሩና በያዙት ጠመንጃ ያሻቸውን ፈጽመው ለሚያድሩ ዘረኞች ጥሎ ለመጥፋትና በኣለም ላይ እንደ አሸዋ ለመበተን የተዘጋጀበት ሃገር፣ ኢትዮጲያ!

የመከራና የሰቆቃው ጥልቀት መዳበሻ ያጣ፣ የሲቃችን ጭላንጭሉ የማይታይበት ሃገር፣ ኢትዮጲያ! እረ እንዴት ነው ነገሩ ይህች የሚገርም የሚያኮራ እንደ እንቁ የሚያበራ ታሪክ የሚያስደንቅ መልከኣ-ምድር፣ የኣየር ጠባይና የተፈጥሮ ሃብት ያላት ሃገር፣ በማንኛውም መመዘኛ ከሲኦል ልዩነት የሌለው ሕይወት የአብዛኛው ሕዝብ እጣ መሆን የቻለው? እንዴት ነው ዛሬ ካለንበት፣ ከውርደትም ከአስከፊ ውርደት በተሞላ አሳፋሪ ሁኔታ ውስጥ መውደቅ የቻልነው? እውን ይህን የአገራችን መከራና ስቃይ፣ በየጊዜው ስልጣን ላይ በመጡ እኩይ መሪዎች ሙሉ በሙሉ አሳበን፣ ይህንን ሁሉ የሰሩት ያደረጉት እነሱ ብቻ ናቸው ብለን ተናግረን ህሊናችን በሰላም ማዋልና ማሳደር ይቻለናልን? እውን ገዥዎቻችን ሃገራችንና ሁላችንንም እንዲያዋርዱ ሳንፈቅድላቸው ብቻቸውን ተነስተው ይህን የውርደት፣ ሃገር የማጥፋት የክህደት፣ የዘረኛነትና የዘራፊነት መርሀ ግብር ማስፈጸም ይችላሉ?

ስለ ሰው ልጆች ነጻነት ብዙ በሚያስተምረው የፍልስፍና ትምህርት ዶክተር የሚል ማዕረግ የተሰጠው የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር ራሱንና ተማሪዎቹን ለደንቆሮዎቹ የወያኔ ካድሬዎችና ሰላዮች በፍርሃት ኣስገዝቶ ለመኖር ሲቆርጥ ኣዋርዱኝ የሚል ፈቃድ ለኣዋራጆቹ መስጠቱ ኣይደለምን? የከፍተኛ ተማሪዎች ተቅዋማትስ? ባገኙት ዕድል የቀድሞ ተማሪዎች መብታቸውን ከማስከበር፣ ዩኒቨርስቲያቸውን የመማሪያና የማስተማሪያ ቦታ ለማድረግ የከፈሉትን መስዋዕትነት እያወቁ፣ ከእዛም በላይ እንደነሱ የእውቀት ብርሃን ለማግኘት ያልታደለውንና በሚከፍለው ግብር የሚያስተምራቸውን ድሃ ህዝብ መብት ለማስከበር ያደረጉትን የተጋድሎ ታሪክ እየሰሙ፣ ምንም ዓይነት ነጻነት በሌለበት፣ የትምህርት ደረጃው በወደቀ ዩኒቨርስቲ መማር፣ በመመረቂያ ወቅት፣ የስራ ወይም ከፍተኛ የውጭ ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ለወያኔ ኢሕኣደግ ታማኝ ባሪያ ሆኖ ለማገልገል በፊርማቸው ሲያረጋግጡ መለስ ዜናዊን አዋርደን የሚል ፈቃድ ኣልሰጠነውም ማለት ይችላሉ? በዜግነቱ ማግኘት የሚገባቸውን መብት የወያኔ ካድረዎችን ጫማ በመሳም፣ እኒህ የቀን ጅቦች በልተው የማይጠቅማቸውን ጉቦ በመስጠት የንግድና ኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የሀገር ውስጥ ብድር የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት የሚሞክረው ነጋዴ፣ የፋብሪካ ጌታ፣ የሕንጻ ተቋዋራጭና ሌላውም ባለሃብት በሃገሩና በራሱ ላይ ለመጣው ውርደት ተጠያቂ ኣይደለሁም ይላል? በዜግነቱ ማግኘት የሚገባውን በሃገሩ የመኖር፣ ንብረትና ቤት የማበጀት መብት ለወያኔ አስረክቦ የወያኔን ችሮታ ለመቀበል በሀገሩና በወገኑ ላይ የሚደርሰውን ስቃይ ወደ ጎን ብሎ የመሬትና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያሳድደው በውጭ አገር የሚኖር ወገናችንስ ራሴን ኣላዋረድኩም ለሀገሬ መዋረድ የድርሻዬን ኣላበረከትኩም ማለት ይችላል? የፖለቲካ ሰዎችስ? የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችስ? ከስሜ፣ ከግል ክብሬ፣ ከግልና ከድርጅቴ ጠባብ ጥቅም በላይ የሃገርና የወገን ጥቅም ይቅደም በሚል፣ ከሸፍጥ፣ ከድህነትና ከማናለብኝነት መንፈስ ውጭ ተባብረውና ሕዝብን አስተባብረው ለመነሳት ባለመቻላቸው የመለስ ዜናዊን ኣገዛዝ ዕድሜ አልቀጠልንም? በስሙ የምንምልለትን ሕዝብ መከራ ኣላራዘምንም ማለት ይችላሉ? ማነው የማይጠየቅ? የመንግስት ሠራተኛው፣ ወታደሩ፣ የተቀረው ሕዝብ፣ ቄሱም ሼኩም የኢትዮጲያ ሕዝብ ለሚገኝበት እጅግ ኣሰቃቂ የሆነ የድህነት ኣዘቅት፣ የመብት ረገጣ፣ የልዑኣላዊነት መገሰስ፣ መለስ ዜናዊ ኣገራችንን እየጋታት መርዘኛና ከፋፋይ የሆነ የዘርና የሃይማኖት ጭማቂ ተጠያቂ ኣይደለንም ማለት ይችላሉ?ደረጃው ይለያይ እንጂ በሃገራችንና በራሳችን ላይ ለሚደርሰው ውርደትና ስቃይ ሁላችንም ተጠያቂዎች፣ ሁላችንም ወንጀለኞች ነን።

ይህ ሃቅ ሺህ ጊዜ ብንፍጨረጨር፣ ምንም ዓይነት ራሳችንን የማጭበርበር ክህሎት ቢኖረን የማናመልጠው ሃቅ ነው። ይህንን በፍጥነት መረዳቱ የመከራ ቀናችንን ለማሳጠር ትልቁ እርምጃ ነውና፣ ሁላችንም እራሳችንን እንጠይቅ። እነዚህ በሃገራችን ላይ የነገሱ ፀረ-ኢትዮጲያና ፀረ- ሕዝብ ኃይሎች የሚፈጽሙትንና የሚያስፈጽሙትን ግፍና በደል ለማስቆም እያንዳንዳችን ራሳችንን ምን አድርጌኣለሁ? ምን እያደረግሁ ነው? ብለን እንጠይቅ።

## መድረክ የወያኔ አገዛዝ የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣውን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

አቶ ገብሩ አስራት በበኩላቸው ኢህአዴግ የሕዝብን መብት እኔ እወስናለሁ ነው የሚለው የሚገርመው ነገር መንግሥትና ሕዝብ አንድ አይደሉም፣ ይህ የአመለካከት ችግር ነው፤ ምክንያቱም ሕዝብ ሲኖር እንደ ግለሰብም ነው፣ ይህን ነው ኢህአዴግም እየጣሰ ያለውና ሕዝቡን በሀገሩ የመንግሥት ጭሰኛ ያደረገው:: የመሬት የባለቤትነት የይዞታ መብት ለገበሬውም ሆነ ለከተማው ሰው ሊከበርለት ይገባል:: ዜጎች ባፈሩት ሃብት- ቤት የመሸጥ፣ የመለወጥ መብት አላቸው:: ቤት አየር ላይ ይሰራ ይመስል መሬቱ የኔ ነው ጣራና ግርግዳ ነው የእናንተ የሚለው ሕዝብን ወደ ድህነት በመክተት በአንድ ለአምስት በመጠርነፍ እያደራጀ እንደ ሊቀመንበር እየሆነ ቤተሰብ ውስጥ ሁሉ ገብቷል:: ኢህአዴግ ኢኮኖሚውን ስቆጣጠር ነው ፖለቲካውን የምቆጣጠረው ብሎ ያስባል:: ከምርጫ 97 በኋላ ያወጣቸው አዋጆች በሙሉ በዚህ ቅኝት የተቃኙ ናቸው:: በዚህም ላይ የመሬት አዋጁ ሃብታም ካልሆነ በስተቀር ደሃ ቤት አይሰራም የሚል አንድምታ አለው፤ ደሃዎችን የበለጠ የሚያደኽይ ነው ብለዋል::

ዶ/ር ሞጋ ፍሪሳ በሰጡት መልስ መሬት ሁልጊዜ ከነፃነት ጋር የተያያዘ ነው፤ የአድዋ፣ የማይጨውም የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት የተደረገው መሬትን ለማስከበር፣ ንብረትነትን ለማረጋገጥ ነው፤ አፍሪካዊያን ቅኝ የተገዙት መሬታቸውን በመነጠቃቸው ነው:: ለዚህም ነው ታግለው ያስለቀቁት:: አሁን መልኩን ቀይሮ በኢንቨስተሮች ሥም ከድሆች ላይ መሬት እየተነጠቀ ነው::

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ደግሞ ይሄ የመሬት ዓዋጅ ሲወጣ ህዝብ አልተወያየበትም፣ በጥድፊያ መንግሥት በጉልበት በህዝቡ ላይ ተግባራዊ ያደረገው ነው፤ ስለዚህ ከተፈጻሚነቱ በፊት ህዝብን አወያይቶ አስፈላጊም ከሆነ ህዝበ ውሳኔ (ሪፍረንደም) መካሄድ ነበረበት ብለዋል::

## የሙስሊሙን ህብረተሰብ በሃይማኖት ለመከፋፈል ሲባል ዘረኛው መለስ ዜናዊ እያካሄደ ያለው ጣልቃገብነት እንዲቆም የሚጠይቅ ተቃውሞ ሠልፍ በደሴ ከተማ መካሄዱ ተዘገበ

በከፋፍለህ ግዛ የአፓርታይድ ፖሊሲ በህዝብ ጫንቃ ላይ ላለፉት 20 አመታት ተንሰራፍቶ የኖረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ የክርስቲያንና የሙስልም ሃይማኖት ተከታዮች በጥላቻ እንዲተያዩ ሲሸርበው የኖረው ተንኮል አንሶት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሙስሊሙ ህብረተሰብ እርስ በርሱ እንዲከፋፈልና ደም እንዲቃባ የሚያደርግ ተግባር እየፈጸመ መሆኑ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት የእምነቱ ተከታዮችን እያስቆጣ መምጣቱን በየጊዜው እየደረሰን ያለው ዘገባ አመለከተ።

ሃይማኖትን እንደፖለቲካ መሳሪያ እየተጠቀመበት ያለው የወያኔ አገዛዝ፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እንዳደርገው ሁሉ በሁሉም ሃይማኖቶች የእምነቱ መሠረት ከሆነው እግዚአብሄር ይልቅ ለመለስ ዜናዊና ለአገዛዙ ታማኝ የሆኑትን የፖላቲካ ካድሬዎች በመሪነት በመሾም የሃይማኖት ተቋማት ጭምር በአገራችን ለሰፈነው አፈና እንደመሳሪያ እንዲያገለግሉ እያደረገ መሆኑ ይታወቃል።

በሙስሊሙ ህብረተሰብ መካከል ወያኔ ሆን ብሎ እየፈጸመ ያለውን ጣልቃገብነት በሃላፊነት የሚያስፈጽመው ሙጀሊስ እንደሆነ የተረዱት የአወሊያ ኮሌጅ ተማሪዎች በቅርቡ ሙጂሊሱ እንዲፈርስ በሰላማዊ ሰልፍ እንደጠየቁና የአዲስ አበባ ከተማ ምዕመናን ባለፈው ሳምንት አርብ ከጁማ ስግደት ቦኋላ የተማሪዎቹን ጥያቄ በመደገፍ መፈክር ሲያስተጋቡ እንደዋሉ መዘገቡ ይታወሳል።

ይህንን የአዲስ አበባውን ሰልፍ ተከትሎ ባለፈው ማክሰኞ በደሴ የሚገኙ ቁጥራቸው ወደ 10 ሺ የሚጠጋ ሙስሊም ወገኖቻችን የአህበሻን አስተምህሮና፣ የወያኔን ጣልቃገብነት በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተዋል።

በደሴ ከተማ ዋናው መስጊድ ግቢ በመገኘት አገዛዙ በሀይማኖት ውስጥ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት እንዲያቆም፣ መጅሊሱ ወይም የእስልምና ጉባኤው ሙስሊሙን የማይወክል በመሆኑ እንዲፈርስ እንዲሁም የአህባሽ አስተምህሮ እንዲቋረጥ የጠየቁት ምዕመናን ጥያቄ ያስፈራቸው የዞኑ የወያኔ ባላስልጣናት፤ ከበላይ አለቆቻቸው ጋር በስልክ ከተነጋገሩ ቦኋላ ወዲያውኑ ሰልፈኞቹ ተወካዮቻቸውን መርጠው እንዲነጋገሩ በመጠየቃቸው 50 ሰዎች ተመርጠው የዞኑ የጸጥታ ሀላፊ፣ የዞን አስተዳዳሪ፣ የደሴ ከተማ ከንቲባና እና ሌሎች 9 የወያኔ ሹሞች ካሉበት ቡድን ጋር ውይይት አካሂዶአል።

በውይይቱ የዞኑ ባለስልጣናት ጉዳዩን ከክልል ባለስልጣናት ጋር ተነጋግረው እስከ ጥር 30 ድረስ መልስ እንደሚሰጡ ለተወካዮች በመግለጽ እስከዚያው ድረስ ግን የአህባሽ አስተምህሮ እንቅስቃሴ እንዲቆም አዘዋል ተብሎአል።

የሙስሊሙ ማህበረሰብ የሀይማኖት መሪዎቹን ራሱ እንዲመርጥ፣ ወያኔ አህባሽን ለማስፋፋት የሚያደርገውን ሩጫ እንዲያቆም፣ የእስልምና ጉባኤ መሪዎች በመንግስት እንጅ በሙስሊሙ ያልተመረጡ በመሆኑ እንዲወርዱና አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ ይጠይቃሉ።

የመጀመሪያዎቹ የነቢዩ መሃመድ ተከታዮች የአገራችንን ምድር ከረገጡበት ዘመን ጀምሮ ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ተቻችሎና ተከባብሮ የኖረውን የእስልምና ሃይማኖት ከምዕራባዊያን በተውሶ በተወሰደ ቋንቋ አንዱን አክራሪ ሌላኛውን ለዘብተኛ በሚል ፍረጃ ወያኔ እየሄደበት ያለው አካሄድ መላውን ህብረተሰብ እንዳስቆጣ ብዙዎች ይናገራሉ።

## እራሱን ልማታዊ መንግሥት ነኝ የሚለው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በኦሮሚያና ሱማሌ ክልል ረሃብ እንዲስፋፋ እያደረገ መሆኑ ተገለጸ

ለፖለቲካ ፍጆታ ሆን ተብሎ በተፈበረከ የእስታቲስቲክስ አሃዝ በየአመቱ 11 ነጥብ 5 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገብኩ ነው በማለት አለም አቀፍ የገንዘብ አበዳሪ ተቋሞችንና ለጋሽ አገሮችን ሲያጭበረብር የኖረው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ በአገሪቱ ታሪክ ድርቅና ረሃብ የማያውቃቸውን የደቡብና የኦሮሚያ ክልሎች በከፍተኛ ረሃብ አደጋ እያስመታ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል።

ለዘመናት በእርሻ ማሳነት በማገልገሉ ምክንያት ለምነቱ በተሟጠጠ የትግራይ ክልል በተደጋጋሚ ተከሰቶ ለነበረው የተፈጥሮ ድርቅና ረሃብ የቀደምቶቹን አገዛዞች በተጠያቂነት ሲወነጅል የነበረው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በደቡብና በኦሮሚያ የሚገኙ የተፈጥሮ ደኖች ሆን ብሎ እንዲወድም በማድረጉ ክልሎቹ በከፍተኛ የተፈጥሮ አየር መዛባት ችግር ውስጥ ገብተዋል።

በመለስ ዜናዊ የህወሃት የበላይነት በ1983 ተቋቁሞ የነበረው የሽግግር መንግሥት ውስጥ ተሳታፊ የነበረው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ከወያኔ ጋር ተጋጭቶ ወደ ትጥቅ ትግሉ ከተመለሰ ቦኋላ በኦሮሚያ የሚገኙ ደኖች የአነግ ታጋዮች ጠለላ ይሆናል በሚል የፖለቲካ ስሌት በታሪካዊ ቅርጽነት ጭምር ሊያዙ የሚገባቸው ሰፋፊ የኦሮሚያና የደቡብ ክልልሎች ደኖች በእሳት እንዲጋይ መደረጉን የሚያስታውሱ ወገኖች፤ በዚያን ወቅት ሆን ተብሎ እንዲወድም የተደረገው የተፈጥሮ ደን በአሁኑ ሰዓት ኦሮሚያናበ ደቡብ የአገራችን ክፍሎች እየተስፋፋ ለመጣው ረሃብና ድርቅ ምክንያት እንደሆነ ይናገራሉ።

ከትውልድ መንደሩ ትግራይ ውጪ ያለውን ሰፊ የአገራችንን ግዛት እንደ አገሩ የማይመለከተው የመለስ ዜናዊ ቡድን ለምና ሰፋፊ የሆነውን የአገራችንን የእርሻ ቦታዎች ለህንድና ለ አረብ ከበርቴዎች በርካሽ ዋጋ በመቸብቸብ ሃብት እያካበተ መሆኑ በተደጋጋሞ መዘገቡ ይታወሳል።

በዚህ ወያኔ ሠራሽ ችግር ምክንያት ቁጥራቸው በትንሹ ከ5 ሚሊዮን በላይ የሆነ በኦሮሚያና በሱማሌ ክልል የሚኖር ህዝብ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚያስፈልገው እየገለጹ ያሉ የሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶች፤ በወያኔ ባለሥልጣናት መረጃ መሠረት የአስቸኳይ ምግብ እርዳታ ፈላጊው ህዝብ ቁጥር ከ3 ሚሊዮን በላይ መሆኑ መታመኑን ይናገራሉ።

ቀደም ሲል በተፈጥሮ ድርቅና ረሃብ ይታወቁ ከነበሩ የአገራችን ክፍሎች ወደ ኦሮሚያና ደቡብ ፊቱን ያዞረው ይህንን ረሃብ አደጋ አስመልክቶ የወያኔ አገዛዝ ቅድመ ማስጠንቀቂያ አህዝ እንደሚያሳየው በመጪዎቹ ስድስት ወራት ከ365 ሜትሪክ ቶን በላይ የምግብ እርዳታ ያስፈልጋል ተብሎአል።

ወያኔ በድህነት ቅነሳ ሥም ከምዕራባዊያን አገሮች የሚደረግለትን የገንዘብ እርዳታ በተገቢው ሥራ ላይ እያዋለ መስሎ ለመታየት በየአመቱ እያስመዘገብኩ ነው የሚለው አሥራ አንድ በመቶ የዕድገት ሪፖርት ለጋሽ አገሮች የምግብ እርዳታ ሲጠየቁ እጃቸውን ወዲያው እንዳይዘረጉ በማድረጉ ለበርካታ ወገኖቻችን ህይወት መቀጠፍ ሰበብ እየሆነ መምጣቱ ታውቆአል።

ሴቭ ዘ ችልደርንና ኦክስፋም የተባሉ አለም አቀፍ ምግባረ ሰናይ ድርጅቶች ሰሞኑን ባወጡት መግለጫ የኢትዮጵያ መንግስት በረሀብ የተጎዱ ዜጎቹን አህዝ አሳንሶ በማቅረቡ በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ህይወት አልፎአል ማለታቸው ይታወሳል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ ፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ጋዜጠኞች በተጨማሪ የወያኔ ፍርድ ቤት በሃሙሱ ችሎት ውሳኔ ያስተላለፈባቸው የኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት ፓርቲ አመራር አባል አቶ ዘርይሁን ገ/እግዚአብሄር በአስራ ሰባት አመትና 50.000 ብር ቅጣት እንዲሁም ወሮ ሂሩት ክፍሌ በ19 አመት ቅጣት እንዲቀጡ ተወስኖበቸዋል።

የፍርደ ገምድሉን ችሎት ውሎ የተከታተለው ዘጋቢያችን እንደገለጸው ዳኛ ተብዬው የወያኔ ጆሌ እንደሻው አዳኔ የፍርድ ውሳኔውን አንብቦ እንደጨረሰ ከተከሳሾቹ መሃል አቶ ዘርይሁን ገ|እግዚአብሄር ወደ ዳኛው በመዞር «እኔ ጥፋተኛ አይደለሁም አንድ ቀን ታሪክ ነፃ ያወጣኛል» ማለቱን ገልጾአል።

የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ በፖለቲካ ተቀናቃኞቹ ላይ የሚያስተላለፈው የበቀል እርምጃ ኢፍትሃዊነት የተሞላበት መሆኑን በማጋለጥ ላይ ያሉት አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች በተወካዮቻቸው አማካኝነት በጋዜጠኞቹና በተቃዋሚ ፖለቲከኞቹ ላይ የተላለፈውን ቅጣት አውግዘውታል።

አጃንስ ፐሬስ የተባለው አለም አቀፉ የዜና ምንጭ እንደዘገበው የአምነስቲ ኢንተርናሽናል የኢትዮጵያ ጉዳይ አጥኚ የሆኑት ክሌር ቤስቶን የፍርዱን ውሳኔ ከሰሙ በኃላ እነኚህ ግለሰቦች በፖለቲካ ምክንያት እነደታሰሩና በአስቸኳይ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፈታት እነደሚኖርባቸው አሳሰበዋል።

እሳቸው እንዳሉት «ግለሰቦቹ በተጠየቁበት ወንጀል ጥፋተኘ መሆናቸውን የሚያሳይ ምንም አይነት ማስረጃ የለም፣ እስር ቤት የተዳረጉት ሀሳባቸውን የመግለፅ ነፃነታቸውን በመተግበራቸው ነው»።

በሂውማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ጥናት አድራጊ ለስሊ ለፍኮም በበኩላቸው፣ «ይህ ብይን ለግለሰቦቹ እጅግ አሳዛኝ፣ ፍትህን አምካኝና ፣ የኢትዮጵያን የፍረድ ተቋማት አቅም የለሽነት ያሳየ ነው» በማለት አጣጥለውታል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የፖለቲካ አፈናውን ህጋዊነት ለማሰጠት እንዲያመቸው በየትኛውም አለም የማይታወቅ ትርጉም ያለው የፀረ.ሽብርተኝነት ህግ አውጥቶ ቁጥራቸው ከ200 በላይ የሆኑ ጋዜጠኞችን፣ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችንና አባላትን እስር ቤት እንዳጎረ ሲፒጄ የተባለው አለማቀፍ ድርጅት አስታውቆአል። እንደሲፒጄ ሪፖርት በአለም ውስጥ ሀገራቸውን ጥለው በተሰደዱ ጋዜጠኞች ብዛት ኢትዮጵያን የሚስተካከል የለም።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ 2 የሲዊዲን ጋዜጠኞችንም በአሸባሪነት ከሶ የ 11 አመት ጽኑ እስራት እንደፈረደባቸውና እስር ቤት አግቶአቸው እንደሚገኝ ይታወቃል።

ዘረኛው መለስ ዜናዊ ከአምስት አመታት በፊት ረሀብ ታሪክ ይሆናል፣ ከ17 አመታት በፊት ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ በቀን ሶስት ጊዜ እንዲበላ እናደርገዋለን ማለቱ ይታወሳል። ወያኔ ስልጣን ላይ ከመጣ ወዲህ በየአመቱ ቁጥራቸው እስከ አሥራ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ወገኖቻችን እየተራቡ በአለም አቀፍ የምግብ እርዳታ ይተዳደራሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከአመት አመት በአለም ባንክና በሌሎችም ለጋሽ ድርጅቶች በሚሰፈርላቸው ስንዴ ብቻ የሚኖሩ ፣ ሴፍቲኔት በሚባለው ፕሮግራም የታቀፉ 7 ሚሊዮን ዜጎች በአገሪቱ ውስጥ መኖራቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ወያኔ በተፈጥሮ ደኖቻችን ላይ በደቡብና በኦሮሚያ ያደረሰውን አይነት ውድመት በአሁን ሰዓት በጋምቤላና በቤኔሻንጉል ክልሎች አጠናክሮ እንደቀጠለ የተለያዩ አለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ ባለሚሎች እየገለጹ ነው።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org